**እንግዶች እንኳን ደህና መጣችሁ!**

## <u>የአርብ ፕሮግራም</u>

## <u>የአርብ ፕሮግራም</u>

**በአርብ ፕሮግራም** እግዚአብሔር ግሩም የጸሎትና የትምህርት ጊዜ እየሰጠን ነው። በተለይም ደግሞ ከፊታችን አርብ ጀምሮ ወንድም ሲሳይ "የእግዚአብሔር መንግስት" በሚል ርእስ ትምህርት ማስተማር ይጀምራል። በዚህ የጸሎት ፕሮግራም ላይ በመገኘት በጸሎትና ቃሉን በመማር እንድንተጋ ቤተ ክርስቲያን ታሳስባለች። እንዲጸለይላችሁ የምትፈልጉ ወገኖችም መሪዎችን ማነጋገር ትችላላችሁ። ጌታ ይባርካችሁ።

## <u>ወገኖችን ማግኘት</u>

በተለያየ ምክኒያት **ወደኋላ የተመለሱ** ወገኖችን ለመፈለግና ለመጎብኘት ሽማግሌዎች እቅድ አውጥተው እየተንቀሳቅሱ ስልሆን የምናውቀውና መጎብኘት አለበት የምትሉትን ስም ለወንድም ጌቱ እንድትሰጡ እናሳስባለን።

"ወደ ውጭም አውጥቶ፡- ጌቶች ሆይ፥ እድን ዘንድ ምን ማድረግ ይገባኛል? ኣላቸው።
እነርሱም፡- በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ እመን አንተና ቤተ ሰዎችህ ትድናላችሁ አሉት።" (ሐዋ. 16፡ 30-31)



- ⇒ የእሁድ ፕሮግራም ይካፈላሉ?
- ⇒ የአርብ ፕሮግራም ይካፈላሉ?
- ⇒ በምጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ይካፈላሉ?
- ⇒ ማገልገል ይፈልጋሉ?
- ⇒ Yeec.org App ጭነዋል?
- ⇒ http://www.yeec.org/ ይጎበኛሉ?

ሽማግሌዎችን ለማግኘት፡-
773-886-0818 (ወ/ም ሲሳይ)
773-507-0194 (ወ/ም አያሌው)
773-910-0485 (ወ/ም ፒተር)
773-961-5332 (ወ/ም ጌቱ)
773-739-0437 (ወ/ም ሰለሞን)

<u>መደበኛ ፕሮግራሞች</u>
እሑድ 1:30 p.m. -- 4:30 p.m.
አርብ 7:00 p.m. -- 9:00 p.m.

| የችካጎ የምስራች ወንጌላዊት ቤተ ክርስቲያን | | Chicago Yemsrach Evangelical Church |
|---|---|---|

"እነሆ፥ ለሕዝቡ ሁሉ የሚሆን ታላቅ ደስታ የምሥራች እነግራችኋለሁና አትፍሩ" ሉቃስ 2፡10




"አንተ የምትተኛ ንቃ ከሙታንም ተነሣ ክርስቶስም ያበራልሃል" (ኤፌ. 5:14)

| Chicago Yemsrach Evangelical Church<br>4455 N. Seeley Avenue<br>Chicago, IL 60625 | መደበኛ ፕሮግራሞች<br>እሑድ 1:30 p.m. -- 4:30 p.m.<br>አርብ 7:00 p.m. -- 9:00 p.m. |
|---|---|
| **November 4, 2018** | **ጥቅምት 25፣ 2011 ዓ.ም.** |

## የእለቱ አገልግሎት መርሃ-ግብር

ጸሎት መሪ................. ወንድም ብርሃኑ አንበሴ

አምልኮ....................... የቤተ ክርስቲያን የአምልኮ ቡድን

ፕሮግራም መሪ .......... ወንድም አያሌው አስፋው

ቃል ............. ዶ/ር ተረፈ አንሼቦ

ማጠቃለያ ................. ፕሮግራም መሪ

### <u>የሳምንቱ ጥቅስ</u>

“እኛ ፍጥረቱ ነንና፤ እንመላለስበት ዘንድ እግዚአብሔር አስቀድሞ ያዘጋጀውን መልካሙን ሥራ ለማድረግ በክርስቶስ ኢየሱስ ተፈጠርን።”

(ፊሊ.. 2:10)

**የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ቡድኖች**

| መሪ | ቀን | አድራሻ |
|---|---|---|
| ወ/ም አያሌው አስፋው | ማክሰኞ | 5030 N. Marine Dr., Chicago, IL 60640 |
| እህት ሰናይት ከበደ | ማክሰኞ | 7200 N. Ridge Ave., Chicago IL 60660 |
| ዶ/ር ተረፈ አንሼቦ | ማክሰኞ | 7526 N. Ridge Blvd., Unit #3W, Chicago IL 60645 |
| ወ/ም ረድኤቱ ካሳ | ማክሰኞ | 7252 W. Everell Ave., Chicago, IL 60631 |
| ወ/ም ሳሚ ኃብተየስ | ሰኞ | 9107 Laramie St. Skokie, IL 60077 |
| ወ/ም ዮናስ ባህሩ | ማክሰኞ | 5523 N. Kenmore Ave., Chicago, IL 60640 |
| | | |

## መልዕክተ ሰንበት

ወ/ም ረድኤቱ ካሳ

### *ሥራህ ምንድር ነው?*

*“...ሥራህ ምንድር ነው? ከወዴትስ መጣህ? አገርህስ ወዴት ነው? ወይስ ከማን ወገን ነህ? አሉት። እርሱም፦ እኔ ዕብራዊ ነኝ፤ ባሕሩንና የብሱን የፈጠረውን የሰማይን አምላክ እግዚአብሔርን አመልካለሁ አላቸው።” (ዮናስ 1፡8-9)*

ብዙ ሰው ስራህ ምንድን ነው ተብሎ ሲጠየቅ “እኔ መሃንዲስ ነኝ”፤ “እኔ ሃኪም ነኝ”፤ “እኔ ሼፍ ነኝ” ወይንም እንዲህና እንዲያ ነኝ ብሎ ይመልሳል። ይህ ጥያቄ ለነብዩ ዮናስ አንድ ጊዜ ቀርቦለት ነበር። በትንቢተ ዮናስ ላይ እንደምናነበው ዮናስ እግዚአብሔር ወደ ነነዌ ሊልከው ወዶ ሳለ እርሱ ግን ከእግዚአብሔር ፊት ኮብልሎ የተርሴስ መርከብ ተሳፍሮ ሲሄድ እግዚአብሔር በባህሩ ላይ ታላቅ መናወጥን አመጣ፤ መርከቢቱም ልትሰበር ቀረበች። የሚደንቀው ነገር ዮናስ ከእግዚአብሔር ሊኮበልል ማሰቡ ነው። ማንም ከእግዚአብሔር መኮብለል የሚችል የለም። እርሱ የሰማይና የምድር ጌታ ነው። መዝሙረኛው ዳዊት አንድ ጊዜ እንደዚህ ዘመረ፡ ከመንፈስህ ወዴት እሄዳለሁ? ከፊትህስ ወዴት እሸሻለሁ? ወደ ሰማይ ብወጣ፥ አንተ በዚያ ነህ፤ ወደ ሲኦልም ብወርድ፥ በዚያ አለህ። እንደ ንስር የንጋትን ክንፍ ብወስድ፥ እስከ ባሕር መጨረሻም ብበርር፥ በዚያ እጅህ ትመራኛለች፥ ቀኝህም ትይዘኛለች። በውኑ ጨለማ ትሸፍነኛለች ብል፥ ሌሊት በዙሪያዬ ብርሃን ትሆናለች፤ ጨለማ በአንተ ዘንድ አይጨልምምና፥ ሌሊትም እንደ ቀን ታበራለችና፤ እንደ ጨለማዋ እንዲሁ ብርሃንዋ ነው። (መዝ. 139፡7-12) ከእግዚአብሔር መንፈስ የትም መሰወር አይቻልም። ይልቁንም ለኛ የሚሻለን ወደ እርሱ መጠጋት ነው።

ዮናስ ሊኮበልል ፈለገ ነገር ግን አልቻለም። ዮናስን ለማግኘት እግግዚአብሔር ባህሩን አናወጠ። መርከቧ ተጨነቀች። ዮናስ ግን በመርከባ የውስጠኛው ክፍል ተኝቶ ነበር። ዮናስ በተገኘ ጊዜና ይህ ታላቅ መከራ ያገኛቸው በእርሱ ምክንያት እንደሆነ ሲገነዘቡ በመርከቧ የነበሩት አዛዦች አምላኩ ስለርሱ ባህርን የሚያናውጥ ይህ ምን አይነት ሰው ነው ብለው የተገረሙ ይመስላሉ። ስለዚህም ጥያቄ ጠየቁት፡ “ሥራህ ምንድር ነው? ከወዴትስ መጣህ? አገርህስ ወዴት ነው? ወይስ ከማን ወገን ነህ?” ጥያቄው የማንነትና የአላማ ጥያቄ ነበር። አገርና ወገን ማንነትን ይገልጣል፤ ስራ ደግም አላማን ይወክላል። ዮናስ የሰጠው መልስ ግሩም ነበር። እኔ እብራዊ ነኝ። ስራዬም እግዚአብሔርን ማምለክ ነው ብሎ መለሰ። ሃገሬ፣ ትውልዴ ማንነቴ ሁሉ የተጠቀለለው በእብራዊነቴ ውስጥ ነው ማለቱ ነው። የእግዚአብሔር የቃል ኪዳን ህዝብ ወገን ነኝ፤ ማንነቴ ያለው ከእግዚአብሔር ጋር ባለኝ ግንኙነት ውስጥ ነው ማለቱ ነው። የተፈጠርኩበት ዋናው አላማ ደግሞ እግዚአብሔርን ማምለክ ነው ማለቱ ነው። ወገኖቼ፡- እኛ የእግዚአብሔር ወገኖች ነን። የሕይወታችን ትርጉም ያለው ከርሱ ጋር ባለን ግንኙነት ውስጥ ነው። የመኖራችን ዋናው አላማም አምልኮ — እግዚአብሔር ማምለክ ነው። እግዚአብሔር ህዝቡን በጸናች ክንድ ከግብጽ ያወጣው፤ ባለንበት ዘመን ደግም በመስቀል ጣር የወለደው ያመልከው ዘንድ ነው።